ማኅበራዊ ጥናት መድረክ
Forum for Social Studies

ጥቅምት 2001 ዓ.ም.

የፖሊሲ ፍሬ ሀሳቦች

ቁጥር 20

# የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ረቂቅ አዋጅ ከሕገ መንግሥቱና ሰብዓዊ መብቶች አኳያ

- የማኅበራዊ ጥናት መድረክ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ-ነክ ምርምሮችን የሚያደርግ ለትርፍ ያልተቋቋመና መንግስታዊ ያልሆነ አገር በቀል ድርጅት ነው።

❋❋❋

- የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፤ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ጋብዞ ያወያያል።

❋❋❋

- በአዲስ አበባ (በ97.1 ሞገድ) እና በአዋሳ (በ100.9 ሞገድ) ከተሞች ኤፍ.ኤም. ራዲዮ ጣቢያዎች ልማት ነክ ጉዳዮችን እያዘጋጀ ያሰራጫል።

❋❋❋

- በድረ-ገጹ በልማት ዙሪያ ውይይቶችን ያካሂዳል።

❋❋❋

- በርዕሱ ዙሪያ ሐሳብ መሰንዘር የምትፈልጉ በኢሜይል አድራሻችን ላኩልን።

## መግቢያ

ላለፉት አምስት ዓመታት መንግስት የሲቪል ማህበረሰቡን የሚያስተዳድር እራሱን የቻለ ህግ ለማውጣት የተለያዩ ጥረቶችን ሲያደርግ ቆይቷል። በእነዚህ ዓመታት የተለያዩ ረቂቅ ህጎች በመንግስት በኩል የቀረቡ ሲሆን በዘርፉ አባላትም እንዲሁ አማራጭ ረቂቅ ህግ ቀርቦ ነበር። የዚህ ጥረት አካል የሆነውና በግንቦት 2000 ዓ.ም. ለሲቪል ማህበረሰቡ ውይይት በፍትሕ ሚኒስቴር የቀረበው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና የማኅበራት ረቂቅ አዋጅ ይገኝበታል።

በዚህ ረቂቅ አዋጅ ላይ የሲቪል ማኅበራት ተወካዮች ውይይት በማድረግ አማራጭ ሀሳቦችን ለመንግስት በተከታታይ አቅርበዋል። ከኢፌዴሪ የፍትህ ሚኒስትር ጋር በተደጋጋሚ፤ ከኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ጋር ደግሞ ሁለት ጊዜ ውይይቶችን አካሂደዋል። እነዚህ ውይይቶችም በሁለቱ ወገኖች መካከል መግባባትና መተማመን ለመፍጠር ካላቸው አስተዋፅዖ ባሻገር ለረቂቅ ህጉ መዳበር ጠቃሚ ለመሆናቸው በተከታታይ የወጡት ረቂቆች ያሳዩት መሻሻል ዓይነተኛ ምስክሮች ናቸው። ይሁን እንጂ ረቂቅ ህጉ አሁን ባለበት መልኩም (3ኛውን ረቂቅ ይመልከቱ) የሲቪል ማኅበረሰቡን ህልውና በእጅጉ የሚፈታተኑና አሳሳቢ የሆኑ ድንጋጌዎችን እንደያዘ ነው።

የዚህ ጽሑፍ ዋነኛ ዓላማ በዚህ ህግ ዙሪያ ከሕገ መንግሥቱና ከሰብዓዊ መብቶች አኳያ እስካሁን ድረስ የተሰሩ ጥናቶችንና በተለያዩ መደረኮች የተካሄዱ ውይይቶችን፣ በሲቪል ማኅበረሰቡ ተወካዮችም ስለረቂቅ አዋጁ ለመንግሥት የቀረቡ አስተያየቶችን ፍሬ ሀሳቦች ጨምቆ በማቅረብ የባለድርሻ ዎችን ግንዛቤ ማዳበር ነው። በጽሑፉ ውስጥ ሲቪል ማኅበር ሲባልም የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን፣ የብዙሃን ማኅበራትን፣ የሙያ ማኅበራትንና ሌሎች የአባሎቻቸውንም ሆነ የሌላውን የሕብረተሰብ ክፍል ጥቅምና መብት ለማራመድ የተ ደራጁትን ፖለቲካዊና አትራፊ ያልሆኑ ድርጅቶች በማካተት ነው ።

## የህጉ መውጣት አስፈላጊነት

የሲቪል ማኅበራትን አስመልክተው በዴሞክራሲያዊ ሕብረተሰቦች ውስጥ የሚወጡ ህጎች ሁለት አበይት ዓላማዎች አሏቸው። እነዚህም የዘርፉን ነፃነት እና ተ ጠያቂነት ማስጠበቅ ናቸው። ህጉ በአንድ በኩል የሲቪል ማኅበራት በብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ ህጎች የተረጋገጡላቸውን ለማንኛ ውም ህጋዊ ዓላማ የመደራጀትና በነፃነት የመስራት መብትን በማስጠበቅ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የሲቪል ማህበራት እንሰራለታለን ወይም ጥቅሙን እናስከብርለታለን ለሚሉት ኅብረተሰብ ያለባቸውን ተጠያቂነት ማረጋገጥ ይኖርበታል።

የህጉ መውጣት አስፈላጊነቱ አጠያያቂ ባይሆንም የብዙ ታዳጊና በቅርቡም ከሶቭየት ሕብረት ተፅዕኖ ተ ላቀው የምዕራቡን የኢኮኖሚ ፈለግ ለመከተል የሚጥሩት የምስራቅ አውሮፓ አገራት ልምድ እንደሚያሳየው በህጉ አወጣጥና ለህጉ መውጣት እንደ መነሻ ምክንያት የሚያገለግሉት እሳቤ ዎች ችግር ማስከተላቸው አልቀረም። ከእነዚህ አገራት ልምድ ማየት እንደሚቻ ለው አንዳንድ መንግስታት ህጎቹን ለማውጣት የሚነሳሱት ከላይ የተ መለከቱትን ሁለት ዓላማዎች ማለትም ተ ጠያቂነትንና ነጻነትን ለማሳካት ከመሞከር ይልቅ፤

- በሥራ ላይ ያለውን ህግ በማጥበቅ የዘርፉን አባላት ምን መስራት እንዳለባቸው እና እንደሌለባቸው በመቆጣጠር በሥራ ነፃነታቸው ላይ ጣልቃ መግባት፣
- ከህዝብ፣ ከመንግስት ወይም ከለጋሽ ድርጅቶች በሚያገኙት ልገሳ ላይ ጥብቅ ቁጥጥርና ገደብ መጣል፣
- ሁሉንም የዘርፉን አባላት በአንድ ዓይነት መንገድ ለማስተዳደር በመሞከር የዘርፉን ህብራዊነት ያለመገንዘብ ችግሮች ይታይባቸዋል።

ጉዳዩን ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ስናየው የሲቪል ማኅበራትን የሚያስተዳድር ህግ መኖር አስፈላጊነቱ አጠያያቂ አይደለም። ይህ ዘርፍ በብዛትና በዓይነቱ እያደገ የመጣ እንዲሁም በኢትዮጵያ የኢኮኖሚና የዴሞክራሲ ዕድገት ውስጥ ያለው ድርሻም እየጨመረ ያለ ዘርፍ ነው። በቅርቡ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ይህ ዘርፍ በብዙ ዎቹ ክልሎች እስከወረዳ ድረስ ካሉ የመስተዳድር አካላት ጋር በተፈጠረ ትብብርና ክትትል በገጠር ልማት፣ በጤናና ትምህርት፣ በአካባቢ ጥበቃ፣ በሥነፆታና ሥነ ተዋልዶ፣ በማይክሮ ፋይናንስ፣ እና ያልተማከለ የአስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተጨባጭ የሆነ አስተ ዋፅዖ በማበርከት ላይ ይገኛል። በደቡብ ክልል ብቻ እስከ አራት ሚሊዮን ሕዝብ ከዚህ ዓይነቱ የመያዶች ሥራ ተጠቃሚ

ለመሆኑ ከክልሉ የተገኛ መረጃ ያሳያል:: በተለይም በውጭ ምንዛሪ ምንጭነት እስከ ቅርብ ጊዜ የአገራችን ዋና የገቢ ምንጭ የነበረው ቡና እ.ኤ.አ. በ2004/5 ያስገኘው 335.2 ሚሊዮን ዶላር ሲሆን መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ግን ምንም ወጪ የሌለበት 444 ሚሊዮን ዶላር ወደ አገሪቱ እንዳስገቡ የብሔራዊ ባንክ መረጃ ያሳያል:: እንዲያውም ዘርፉ በየዓመቱ የሚያስገባው ገቢ መጠን ከአገሪቱ ዓመታዊ የበጀት መጠን ጋር ሲነፃፀር ሩቡን ያህል እንደሚደርስ ከመረጃዎቹ መረዳት ይቻላል::

ይሁን እንጂ ዕድገቱን ተከትሎ ዘርፉ የሚሰራበትን የህግና የፖሊሲ ማዕቀፍ የማሻሻል ሥራ ገና በጅምር ላይ ያለ ነው ማለት ይቻላል:: ይህ ዘርፍ የሚተዳደረው በአፄው ዘመነ መንግስት በወጡ ህግና ደንብ ነው:: በአጠቃላይ በኢትዮጵያ አዲስ ህግ መውጣትን የግድ የሚሉ በርካታ ምክንያቶች ሲኖሩ ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ፤

- የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 31 ላይ የተመለከተውን የሰዎችን የመደራጀት መብት ተግባራዊ ለማድረግ፣
- ኢትዮጵያ መሠረታዊ መብቶችን የሚያስከብሩ የተለያዩ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነት ፈራሚ በመሆኗ እነዚህን ስምምነቶች ተግባራዊ ለማድረግ፣
- አሁን በስራ ላይ ያለው የህግ ማዕቀፍ የሲቪል ማህበራትን ነፃነትና ተጠያቂነት ለማስጠበቅ ዘርፉ ከደረሰበት የዕድገት ደረጃ አንፃር በቂ ሆኖ ያለመገኘቱ፣ ናቸው::

ዘርፉን በሚመለከት እራሱን የቻለ የፖሊሲ ሠነድ ባይኖርም የአገሪቱ ትላልቅ የፖሊሲ ሠነዶች ሲቪል ማህበራት በልማትና ዴሞክራሲ እድገት ውስጥ ያላቸውን ሚና ስለሚያነሱ ይህንን ሚናቸውን መጫወት እንዲችሉና የመንግስት የልማትና የዴሞክራሲ አጋር እንዲሆኑ ለማስቻል ምቹ ህግ ያስፈልጋል::

## የህጉ በጎ ጎኖች

ለውይይት የቀረበው ረቂቅ ህግ ከላይ የተመለከቱትን ዓላማዎች ለማሳካት የሚያስችሉት ምን ያህል ጠንካራ ጎኖች እንዳሉት መመልከቱ ጠቃሚ ነው::ይህ ለውይይት የቀረበው የ2000 ዓ.ም. ረቂቅ ህግ እስከ አሁን ድረስ 3 ጊዜ መከለሱን ለማወቅ ተችሏል:: በዚህ ሂደትም ጥቂት አበረታች ማሻሻያዎች ተደርገዋል:: አሁን ባለው ይዘቱ የሚከተሉትን ነጥቦች እንደጠንካራ ጎን ማስቀመጥ ይቻላል:: ከሁሉ በላይ ግን በህጉ ውስጥ ያሉ ሊሻሻሉ የሚገባቸው ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆነው የሲቪል ማኅበራትን ለማስተዳደር እራሱን የቻለ ህግ መውጣቱ በራሱ አበረታች እርምጃ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል:: ወደ ዝርዝር ነጥቦቹ ስንሄድም፤

- ዘርፉን የሚያስተዳድር እራሱን የቻለ በኤጀንሲ ደረጃ ያለ ተቋም እንዲመሰረት መደረጉ፣
- በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ሥራዎቻቸውን በማስተባበር ዓላማ ህብረት መፍጠር እንዲችሉ መመልከቱ፣
- በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት በኤጀንሲው ፈቃድና ከዓላማቸው ጋር በሚያያዝ የገቢ ማስገኛ ስራ ላይ መሰማራት እንደሚችሉ መደንገጉ፣ የህጉ ዋና ዋና በጎ ጎኖች ሆነው ሊታዩ ይችላሉ::

## በህጉ ዙሪያ ያሉ ዋና ዋና ችግሮች

ከላይ የተጠቀሱት ጠንካራ ጎኖች እንደተጠበቁ ሆነው በቀረበው ረቂቅ ህግ ዙሪያ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው በርካታ ጉዳዮች አሉ:: ከዚህ ቀጥለን ዋና ዋና የሚባሉትን ችግሮች እንመለከታለን::

### *1. ህጉ መሠረት የሚያደርገው የራሱ የሆነ ፖሊሲ የለውም::*

የተለያዩ አገራት በተለይም የቅርብ ጎረቤታችን የኬንያ ልምድ እንደሚያሳየው መንግስት ዘርፉን አስመልክቶ የፖሊሲ አቅጣጫ ሊኖረው ይገባል:: በዚህ የፖሊሲ ሠነድ ላይ የሲቪል ማኅበረሰቡ ዘርፍ በልማትና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ውስጥ ሊኖረው የሚችለው ሚና እና ይህንን ሚና መጫወት እንዲችል ለነፃነቱና ተጠያቂነቱ መረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ምን እንደሆኑ በግልፅ ተለይቶ መታወቅ አለበት:: በአገራችን ምንም እንኳን የሲቪል ማኅበራት በልማትና ዴሞክራሲ ግንባታ ቀላል የማይባል አስተዋፅዖ ማበርከታቸው ቢታወቅም ይህንን ዘርፍ አስመልክቶ የወጣ እራሱን የቻለ የመንግስት የፖሊሲ ሠነድ የለም:: በዚህ ረገድ የተሞከረ ነገር ቢኖር በአቅም ግንባታ ሚኒስቴር አማካኝነት የዘርፉን አቅም ለማጠናከር የሚያስችል ረቂቅ ሠነድ መዘጋጀቱ ነው:: ይህ ሠነድ ምንም እንኳን የተሟላ ሠነድ ባይሆንም ከረቂቅነቱ አልፎ ወደ ተግባር ሊሸጋገር አልቻለም::

አሁን በረቂቅ ህጉ ላይ የሚታዩት ብዙዎቹ ችግሮች የፖሊሲ እጦት የወለዳቸው መሆኑን መረዳት አያስቸግርም:: ይህ ሠነድ ባለመኖሩ ከእያንዳንዱ ድንጋጌ ጀርባ ያለው ዓላማ ምን እንደሆነ ለማወቅ አስቸጋሪ ሆኗል:: መንግስት ከዚህ ዘርፍ የሚጠብቀው ምንድን ነው? ዘርፉ በልማትና በዴሞክራሲ ግንባታ ውስጥ የሚኖረው ሚና በመንግስት ዕይታ ምንድነው? ዘርፉ የሚፈለግበትን አስተዋፅዖ እንዲያደርግ ምን ዓይነት የአቅም ማጎልበት ድጋፍና ማበረታቻ መንግስት ያደርግለታል? በመንግስት እና በዘርፉ መካከል ሊኖር የሚገባው ግንኙነት ምን መምሰል አለበት? የዘርፉን የተለያዩ አባላትና ክፍሎች መንግሥት በእኩልነት ለማስተናገድ ምን ዓይነት ስልት ይከተላል? እነዚህንና ሌሎች በርካታ ጥያቄዎችን ረቂቅ ህጉን ብቻ በመመልከት መመለስ አይቻልም:: የረቂቅ ህጉ ዓላማ መሆን የነበረበት የዘርፉን መብትና ነፃነት፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት ከሀገሪቱ ህገ መንግስት አኳያ ማስጠበቅ ነበር::

### *2. ህጉ ከሕገ መንግስቱ ጋር የሚጋጩ ድንጋጌዎችን ይዟል::*

በረቂቅ ህጉ ላይ ትኩረት ከሚያስፈልጋቸው ነጥቦች ውስጥ በዋነኛነት ከሕገ መንግስቱ ጋር የሚጋጩት የአዋጁ ድንጋጌዎች ናቸው:: ከእነዚህም:-

- በህገ መንግስቱ አንቀፅ 31 ላይ **ለማንኛውም ሰው** የተረጋገጠውን የመደራጀት መብት የረቂቅ ህጉ መግቢያ መብቱን **ለዜጎች** ብቻ ገድቦ አስቀምጧል::
- የህገ መንግስቱ አንቀፅ 31 ማንኛውም ሰው **ለማንኛውም ህጋዊ ዓላማ** መደራጀት ይችላል እያለ ረቂቅ ህጉ የድርጅቶችን የገቢ ምንጭ መሠረት በማድረግ ከገቢያቸው ከ10% በላይ ከውጪ ምንጭ የሚያገኙ ድርጅቶች ወይም የውጭ አገር ድርጅቶች በህፃናት፣ በሴቶች፣ በአካል ጉዳተኞች፣ በሰብዓዊ መብት፣ በግጭት አፈታትና የፍትህ አካላትን በማጠናከር እና በመሳሰሉት መብት-ነክ የአድቮኬሲ ሥራዎች ላይ እንዳይሳተፉ ይከለክላል:: እነዚህ ሥራዎች ግን በሕገ መንግስቱ ላይ እንደተመለከተው ህጋዊ ዓላማዎች ከመሆናቸውም በላይ በማንኛውም ሰው ሊሰሩ የሚችሉ ሥራዎች ናቸው::
- የህገ መንግስቱ አንቀፅ 37 ፍትህ የማግኘት መብትን

ለማንኛውም ሰው አረጋግጧል:: ይሁን እንጂ የረቂቅ ህጉ አንቀጽ 105 ይህንን መብት ለውጭ ድርጅቶች እና ከገቢያቸው ከ10 ከመቶ በላይ ከውጪ ለሚያገኙ ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች (አባሎቻቸው ኢትዮጵያውያን ቢሆኑም) ይነፍጋል:: እነዚህን ድርጅቶች አስመልክቶ ህጉ የሚፈቅደው አስተዳደራዊ ውሳኔ ብቻ ከመሆኑም በላይ ጉዳያቸው በፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ሥልጣን ባለው ነፃ አካል ፊት ሊቀርብ እንደማይችል አስቀምጧል::

- የህገ መንግስቱ አንቀፅ 37 ፍትህ የማግኘት መብትን ሲያረጋግጥ በፍርድ ሊወሰን በሚገባው በማኛኛውም ጉዳይ ላይ ነው:: ህገ መንግስቱ በዚህ መብት ለመጠቀም የጉዳዮችን ዓይነት ገድቦ አላስቀመጠም:: ይሁን እንጂ ረቂቅ ህጉ የዳኝነት ሥልጣን ባልተ ሰጠው የአስተዳደር መ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ በህግ ስህተት ላይ ካልሆነ በፍሬ ጉዳይ ስህተት ላይ ለፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረብ እንደማይቻል ይደነግጋል::

- የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 32(1) እና 41(1,2) ማንኛ ውም ዜጋ በማንኛውም የአገሪቱ ክፍል የመንቀሳቀስና የመረጠውን ሥራ የመስራት መብትን እውቅና ሲያረጋግጥ በዚህ መብት ለመጠቀም በቡድንና በተናጠል ወይም በሥራ ዓይነት በሚል ምንም ዓይነት ልዩነትና ገደብ አያስቀምጥም:: የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 70(5) ግን የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማኅበሩ ስያሜ አገር አቀፋዊ ወይም ፌዴራላዊ ሆኖ የአባላት ጥንቅር ወይም የሥራ ቦታው ቢያንስ የ5 ክልሎች ውክልና የሌለው ከሆነ ህጋዊ ሆኖ ለመስራት ምዝገባን ስለሚከለክል ይህ ድንጋጌ የዜጎችን በፈለጉት መልክ ተደራጅተው በመ ረጡት የአገሪቱ ክፍል የመንቀሰቀስና የመረጡትን ሥራ የመስራት መብትን በተዘዋዋሪ ይገድባል::

### *3. ህጉ ከውጭ የሚገኝ ገቢን አስመልክቶ ያስቀመጠው ገደብ የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ አይደለም::*

ኢትዮጵያውያን በጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማኅበራት ከገቢያቸው ከ10 ከመቶ በላይ ከውጭ ምንጭ እንዳይጠቀሙ ህጉ የጣለው ገደብ ኢትዮጵያዊ የሚባል ድርጅት ወይም ማኅበር ቁጥሩ እጅግ እንዲቀንስ ወይም እንዲጠፋ ካልሆነ በቀር አሁን ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ አይደለም:: አሁን ባለው የኑሮ ውድነት ምን ያህሉ የኢትዮጵያ ህዝብ ከራሱ የዕለት ፍጆታ ተርፎት ሌሎች ሰዎችን በቋሚነት ለመርዳት የሚያስችል የኢኮኖሚ አቅም አለው? እንዲሁም በአገራችን እንዲህ ዓይነቱ የልገሳ ባህል አለ ወይ? ለሚለው አጥጋቢ መልስ በሌለበት ሁኔታ ኢትዮጵያውያን ድርጅቶችን ከውጭ ምንጭ ከ10% በላይ ገንዘብ ወይም ሌላ እርዳታ መቀበል አትችሉም ማለት ህልውናቸውን ከማጥፋት የተለየ አይደለም::

በመብት-ነክ ጉዳዮች ዙርያ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች ሁሉ ለስራቸው በአብዛኛው በአባላት ነፃ ጉልበትና ተ ሳትፎ ወይም መዋጮ ይወሰኑ ማለትም ጠንካራ ድርጅታዊ ተቋምና የፋይናንስ አቅም አይኑራቸው፤ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ወስጥ የሚኖራቸው ሚና፤ የስራ አድማስና ውጤት የማምጣት አቅምም ይገደብ ከማለት የተለየ አይሆንም::

### *4. ህጉ በኢትዮጵያውያን ድርጅቶች ላይ ከውጭ በሚገኝ እርዳታ ላይ ማዕቀብ ሲጥል በአገር ውስጥ የፋይናንስ አቅማቸውን እንዲያጠናክሩ የፈጠረው የተመቻቸ ሁኔታና ተጨባጭ አማራጭ የለም::*

የሌሎች አገራት ልምድ እንደሚሳየው የሲቪል ማኅበራት ከውጭ በሚገኝ ገቢ ላይ ጥገኛ እንዳይሆኑ የተለያዩ የገቢ ማበረታቻዎች በአገር ውስጥ ይደረግላቸዋል:: በረቂቅ ህጉ ላይ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት በገቢ ማስገኛ ሥራ ላይ እንደሚሰማሩ ቢጠቅስም በዚህ መብት የመጠቀም እድላቸውን ህጉ ራሱ መልሶ አጥቦታል:: በቅድሚያ በገቢ ማስገኛ ስራ ላይ ለመሰማራት የኤ ጀንሲው ፈቃድ ያስፈልጋል:: ቀጥሎ ሥራው ከድርጅቱ ዓላማ ጋር ተያያዥነት ያለው መሆን አለበት:: በተ ጨማሪም ለድርጅቱ ከሌላው ነጋዴ የተለየ ጥበቃ እንደማይደረግለት እና እንደማኛኛውም የንግድ ሥራ ታይቶ አግባብ ባላቸው ህግ መሠረት እንደሚተዳደር ይገልፃል:: ከዚህ ሌላም ከመደበኛ ስራቸው ጋር በተ ቀጥላነት የተጎዳኙና ለትርፍ ሳይሆን ለመደጎሚያነት በምርት ወይም በአገልግሎት ሽያጭ ወይም በኪራይ መልክ ለሚያገኙት የገቢ ምንጭም ያለምንም ልዩነት የንግድ ፈቃድ ማውጣትን ያስገድዳል:: ስለዚህ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት በገቢ ማስገኛ ሥራ ላይ የተቀመጡትን ገዳቢ መስፈርቶች አልፈው መሰማራት እንደሚችሉ ከመገለፁ ውጪ የተደረገ የተለየ ጥበቃ የለም::

በሌሎች አገሮች፣ ለምሳሌ ጋና የሚታየው በመንግስት በኩል የሚሰጥ ድጋፍ ነው:: ረቂቅ ህጉ መንግስት ለሲቪል ማህበራት ሊሰጠው ስለሚችለው የድጋፍ ዓይነት የሚገልፀው ነገር የለም:: የሌሎች አገሮች ልምድ እንደሚያሳየው ሲቪል ማኅበራት ከአንዳንድ የታክስ ክፍያዎች ነፃ ይደረጋሉ:: ለምሳሌ ከተ ጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ፣ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ላይ ተ ሰማርተው ከሚያገኙት ትርፍ ግብር ነፃ መሆን፣ እንዲሁም ለሥራቸው አስፈላጊ የሆኑ ዕቃዎችን ከቀረጥ ነፃ ከውጭ አገር ማስገባት እና የመሳሰሉት ድጋፎች ይደ ረግላቸዋል:: ነገር ግን ረቂቅ ህጉ እንደዚህ ዓይነት መማበረታቻዎችን እንኳን ሳያስቀምጥ በተለይ በኢትዮጵያውያን መብት-ተኮር ድርጅቶች ላይ ከውጭ ምንጭ በሚያገኙት ገቢያቸው ላይ ከፍተኛ ገደብ ማድ ረጉ ተገቢ አይደለም::

### *5. ህጉ ኢትዮጵያ በፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች፣ የመግባቢያ ሠነዶች እና በአገሪቱ ታላላቅ የፖሊሲ ሠነዶች ላይ ሲቪል ማህበራትን የሚደግፉ መርሆችንና ዕሳቤዎችን አላገናዘበም::*

የመደራጀት መብትን አስመልክቶ ግዴታዎችን የያዙ የተ ለያዩ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችን ኢትዮጵያ ፈርማለች ወይም ተቀብላለች:: ከእነዚህም ውስጥ አለም ዓቀፉ የሰብዓዊ መብት መግለጫ፣ ዓለም አቀፉ የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን እና የአፍሪካ ህዝቦች የሰብዓዊ መብቶች ቻርተር ይገኙ በታል:: እነዚህ ሠነዶች የመደራጀት መብትን ለማንኛ ውም ሰው ዜግነትን መሠረት ሳያደርጉ ያረጋገጡ ሲሆኑ ሠነዶቹ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 9 እና 13 መሠረት የአገሪቱ የህግ አካል ናቸው:: በተጨማሪም ኢትዮጵያ የኮቶኑ ስምምነት፣ የአፍሪካ ሕብረት ማቋቋሚያ ስምምነት እና የኔፓድ ፈራሚ አገር ናት:: እነዚህ ሠነዶች የሲቪል ማኅበራት በልማትና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ውስጥ ያላቸውን ቁልፍ ሚና ከማስቀመጣቸውም በላይ የኢትዮጵያ መንግስት ለተ ቋማቱ ተገቢ ጥበቃ እንዲያደርግ ያስገድዳሉ::

ከእነዚህ ዓለም አቀፍ ሠነዶች በተጨማሪ በአገሪቱ ውስጥ ካሉት ታላላቅ የፖሊሲ ሠነዶች ውስጥ አንዱ በተፋጠነና ዘላቂ ልማት ድህነትን የማጥፋት ዕቅድ የሲቪል ማኅበረሰቡ ለእቅዱ ስኬት የሚኖረውን ሚና ያመለክታል:: ይሁን እንጂ ረቂቅ ህጉ ዘርፉ በልማት እና በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ያለውን ሚና ከማስፋት ይልቅ በማጥበብና በመቆጣጠር ላይ ያተኩራል::

### *6. ህጉ መብት ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የሚሰሩ ሥራ ዎችን አያበረታታም::*

በረቂቅ ህጉ አንቀጽ 14 ላይ ያለው ገደብ ከመብት እና ከመልካም አስተዳደር ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሥራ ዎች ከገቢያቸው 10% ብቻ ከውጭ ምንጭ ለሚያገኙ

ኢትዮጵያውያን ድርጅቶች ብቻ ሲፈቅድ በዚህ ሥራ ላይ የተሰማሩትንና የውጭ የገቢ ምንጫቸው ከ10% በላይ የሆኑትን አብዛኞቹን ሌሎች ድርጅቶች በመስኩ እንዳይሳተፉ ያግዳል:: አሁን በዓለም ላይ ያለው የልማት አስተሳሰብ እና መርሕ ዘላቂነትን (sustainability) እና ራስን ማስቻልን (empowerment) መሠረት ያደረገ ነው:: የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታንና የልማት ሥራን ያስተሳሰረ ነው:: የሁሉም የሲቪል ማኅበራት በሁሉም የልማትና የዴሞክራሲ ዘርፎች እኩል የመሳተፍ ዕድል ማግኘት ያለባቸውም ከዚህ ዕሳቤ በመነሳት ነው::

የማንኛውም ማኅበረሰብ አባላት በሌሎች ዕርዳታ ላይ ሁሌም ጥገኛ እንዳይሆኑ፣ እነሱንና ሕይወታቸውን በሚመለከት ሁሉ የሚፈልጉትንና ቅድሚያ የሚሰጡትን የመወሰን፣ ሕይወታቸውን ለማሻሻልና ደህንነታቸውን ለማረጋገጥ በሚደረግ የፖሊሲና የዕቅድ ቀረፃ፣ የአፈፃፀምና የአስተዳደር ሂደት ውስጥ ንቁ ተሳታፊ የመሆንና እንዲሁም የጉዳዩ ባለቤት የመሆን መብት እንዳላቸው መረዳት ያስፈልጋቸዋል:: በሕገ መንግሥቱና አገሪቱ ፈርማ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት የተረጋገጡትን መብቶቻቸውን አውቀው ጥቅሞቻቸውን ለማስከበርና ዘላቂ ልማታቸውን ለማረጋገጥ ለዚህ የሚሆናቸው የግንዛቤ ማዳበሪያ ትምህርት፣ ወቅታዊና ለየአካባቢያቸው ፋይዳ ያለው መረጃና ለጥረታቸው ስኬት አቅማቸውን የሚያጎለብትላቸውና ድምፃቸውን የሚያጎላላቸው ነፃ ድርጅታዊ መዋቅር ያስፈልጋቸዋል:: የሲቪል ማኅበራት ጥረት ይህን ለማሟላት ነው:: ይህ ዘርፈ-ብዙ የልማት ጥረት በአገልግሎት መስጠት ሥራና በአድቮኬሲ ሥራ፣ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና በልማት ሥራ መካክል ያለውን መነጣጠል በማስቀረት መብት-ተኮር የልማት ስልት (Rights Based Approach) በመባል በኢትዮጵያና በሌሎችም አገሮች በሚንቀሳቀሱ የሲቪል ማኅበራት እየተተገበረ ውጤታማ መሆኑን አረጋግጧል::

ይሁን እንጂ አሁን በአንቀፅ 14 መሠረት በመብት ነክ የአድቮኬሲ ሥራ ላይ የተደረገው ገደብ በዚህ በኩል ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩ አይቀርም:: ይህ በመሆኑም ይህ ህግ አሁን ባለው ሁኔታ ቢፀድቅ የሲቪል ማኅበራት በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ላይ ያላቸውን ሚና ብቻ ሳይሆን በልማት መስክ የሚያበረክቱትን ከፍተኛ አስተዋፅዖም ይገድባል፤ የልማቱን ዘላቂነትም ይፈታተናል::

### የማሻሻያ ሀሳቦች

- የሲቪል ማኅበራትን ሚና፣ ከመንግስት ጋር ያላቸውን ግንኙነት፣ በሥራቸው ላይ ያለባቸውን ተጠያቂነት፣ ሥራቸውን በተፈለገው ጥራትና መጠን መሥራት እንዲችሉ የሚደረግላቸውን ጥበቃ እና የመሳሰሉትን የሚሳይ የፖሊሲ ሠነድ መኖር አስፈላጊ ነው::
- የሲቪል ማኅበራትን ለማስተዳደር የሚወጣው ህግ ፖሊሲውን፣ ህገ መንግስቱን፣ ኢትዮጵያ የፈረመቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና ሌሎች ዘርፉን የሚመለከቱ የፖሊሲ ሠነዶችን መሠረት ማድረግ ይኖርበታል::
- የሚወጣው ህግ የሲቪል ማኅበራትን ተጠያቂነት ብቻ ሳይሆን ለሥራቸው ስኬት የሚያስፈልጋቸውን ቅድመ ሁኔታዎችንም የሚያመቻች መሆን አለበት::
- በህገ መንግስቱ አንቀጽ 31 መሰረት የሲቪል ማኅበራት የአገር ውስጥና የውጭ አገር የሚል ልዩነት ሳይደረግባቸው በማንኛውም ሕጋዊ ዓላማ ላይ የመሰማራት መብታቸውን ህጉ ሊያስጠብቅ ይገባል::
- በአገሪቱ ውስጥ የሲቪል ማኅበራትን እንቅስቃሴ ሊደግፍ የሚችል ኢኮኖሚያዊ አቅም እስኪፈጠር ማህበራቱ ለዓላማቸው ማስፈጸሚያ የሚውል የውጭ ዕርዳታ መቀበል እንዲችሉ ህጉ ተገቢውን ጥበቃ ማድረግ ይኖርበታል::
- መንግሥት የሲቪል ማኅበራት በውጭ እርዳታ ላይ ጥገኛ መሆን የለባቸውም የሚል አቋም ካለው ከምዕዋት ያለፈ የበጎ አድራጎትና የልግስና ባሕል ሥር ባልሰደደበት ኅብረተሰብ ውስጥ ይህን በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ህልውናቸው ሳይናጋ ማሟላት ስለሚያስቸግር በፋይናንስ ራሳቸውን የሚችሉበት በቂ የሽግግር ጊዜ እንዲሰጥ፣ ከአገር ውስጥ ምንጮች ገንዘብ ለማሰባሰብና ለሥራ መንቀሳቀሻ በቂ ጥሪት ለማፍራት የሚያስችል ምቹና ዘርፈ-ብዙ ማዕቀፍ ለሲቪል ማኅበረሰቡ እንዲዘጋጅና ይህም ማዕቀፍ በቢሮክራሲ ያልተወሳሰበና ለገቢያቸው መደጎምያ እንዲሆን በመረጡት የገቢ ማስገኛ ሥራ መሰማራትን፣ ከዚህ ገቢያቸውና ከሚፈፅሙት ግዢ ላይ ከታክስ ነፃ መሆንን፣ የአገር ውስጥ ለጋሾችን ለማብረሰናይ ሥራ የገንዘብ ድጋፍ እንዲያደርጉ የሚያበረታታ የግብር ቅናሽን እንዲያካትት ማድረግ ያስፈልጋል::
- የሚወጣው ህግ የሲቪል ማኅበራትን በማንኛውም ህጋዊ የሆነ ሥራ ላይ ያለገደብ የመሰማራት መብት ሊያስጠብቅ ይገባል:: የገቢ ምንጭንና ዜግነትን መሠረት በማድረግ ልዩነቶችን ሊፈጥር አይገባም::
- ህጉ ፍትህ የማግኘት መብትን በማስጠበቅ በየትኛውም አስተዳደራዊ ውሣኔ ላይ ሲቪል ማኅበራት ለፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብታቸውን ሊያስከብር ይገባል::
- የሲቪል ማኅበረሰቡ ራሱን በራሱ ማስተዳደርና መቆጣጠር እንዲችልና ተጠያቂነትና ግልፅነት ያለው አሰራር መስፈኑን ለማረጋገጥ ሁሉም የሲቪል ማኅበራት ተገዢ የሆኑለትና በሁሉም ላይ እኩል ተፈፃሚነት ያለው የሥነ ምግባር መመሪያ በሥራ ላይ እንዲውል ዕውቅናና የሕግ ኃይል የሚሰጠው አንቀጽ በአዋጁ ውስጥ ማካተት ያስፈልጋል::

**(ደበበ ኃይለገብርኤል)**


ምስጋናና ማሳሰቢያ

ይህ ሰነድ የታተመው በአውሮፓ ሕብረት የገንዘብ ድጋፍ ነው:: ለሰነዱ ይዘት ሙሉ ኃላፊነቱ የደራሲው ሲሆን በምንም ሁኔታ የአውሮፓን ሕብረት አቋም እንደሚያንፀባርቅ ተደርጐ መወሰድ የለበትም::



አድራሻ: የማኅበራዊ ጥናት መድረክ ♦ ፖ.ሳ.ቁ 25864 ኮድ 1000 ♦ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ስልክ: 011-629 78 88/91♦ ፋክስ: 011-629 78 89
ኢሜይል: fss@ethionet.et ♦ ድረ ገፅ: www.fssethiopia.org.et